# Statewide Specialist Clinical Consultation Service

*A service provided by the Queensland Transcultural Mental Health Centre*

## ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት (AMHARIC)

### ሁሉንአቀፍ የህክምና አመክሮ አገልግሎት ምንድን ነው?

ይህ ክፍለ ሃገር አቀፍ የሆነ ልዩ የጤና አመክሮ በኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና አገልግሎት ማእከል፤ እንግሊዘኛ የመናገር ችሎታ ለሌላቸው ግለሰቦች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ይህ አጋልግሎት የነፃ አገልግሎት ነው።

### ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎትን ማን ሊጠቀምበት ይችላል?

ስለአእምሮ በሽታ የግል፤ የቤተሰብ አባል ወይንም ጓድኛ ላይ ስጋት ካለዎት ማእከሉን ያነጋግሩ።

### ይህ አገልግሎት እኔን እንዴት ሊረዳኝ ይችላል?

ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት የአእምሮ በሽታን በተመለከተ ስለተጨነቁበት ጉዳይ መግለጫና ምክር በመስጠትና ከሚመለከታቸው አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት እርዳታ ያደርጋል። ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለገዎት፤ የአእመሮ ጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ወይንም ባህልዎንና ቋንቋዎን ከሚያውቅ የአእምሮ ጤና ሠራተኛ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ፤ የአእምሮ ጤና ችግርዎን እንዲቋቋሙ የአጭር ጊዜ እርዳታ ያደርግልዎታል።

የአእምሮ ጤና ሠራተኛው ቀጥሎ በተመለከቱት መንገዶች ይረዳዎታል፤

- ባህላዎ ጉዳዮችን ለአእምሮ ጤና አገልግሎቱ ማስረዳት፤
- በሚደረግልዎ ህክምናና እንክብካቤ ጉዳይ ላይ ሃሳብዎን እንዲሰጡ መርዳት፤
- የአእምሮ ጤናዎን በተመለከተ፤ በሚናገሩት ቋንቋ ምክክር ለማድረግ ከእርስዎ ጋር መገናኘት፤
- የአእምሮ ጤናዎን ጉዳይ ለቤተሰብ አባላትዎ ማስረዳትና፤
- ከአእምሮ በሽታ ችግርዎ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የአጭር ጊዜ ድጋፍ ወይንም አመክሮ መስጠት ናቸው።

### ከዚህ የተለየ ምን እርዳታ ታደርጋላችሁ?

ማእከሉ የአእምሮ በሽታና ተመሳሳይ ችግሮችን በተመለከተ ብዙ የጽሑፍ መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች አዘጋጅቷል። ስለምልክቶቹ፤ ስለህክምናው፤ ስለመድሃኒቱና በአካባቢው ስለሚገኙት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችና ስለመሳሰሉት ለመወያየት ከፈለጉ፤ ለማእከሉ መደወል ይችላሉ።

### አገለግሎቱ ምስጢር ይጠብቃል?

አዎን፤ የአእምሮ ጤና ሠራተኞቻችን፤ እንደሌሎቹ የጤና አገልግሎቶች ሁሉ፤ ጥብቅ በሆነ ምስጢር የመጠበቅ የስርአት ግዴታ አለባቸው። ስለሆነም፤ ያለፈቅቃድዎ ስለጉዳይዎ ከማንም ጋር መወያየት አይችሉም።

### ከሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አግልግሎት ምን አይነት አገልግሎት አገኛለሁ ብዬ እጠብቃለሁ?

በክብር፤ ብኩራትና ግለኝነትዎን ከቁጥር በማስገባት፤ እንዲሁም ሃይማኖትዎንና ባህልዎን በማገናዘብ ህክምና እንዲደርግልዎት መጠበቅ ይችላሉ።

ከአእምሮ ጤና ሠራተኞችም ሆነ ባህልዎን ወይንም ቋንቋዎን ከሚያውቅ ሰው ጋር ከመገናኘትዎ በፊት ፈቃድዎን በጽሑፍ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።

### ከመሥሪያ ቤቱ ጋር እንዴት መገናኘት እችላለሁ?

ብሪዝበን ከተማ ከሆኑ፤ በስልክ ቁጥር (07) 3167 8333 ወይንም ከብሪዝበን ከተማ ውጪ ከሆኑ 1800 188 189 መደወል ይችላሉ። ከሰኞ እስከ አርብ 8:30 ጠዋት ጀምሮ እስከ 4:30 ከሰአት በኋላ ደውለው የህክምና አገልግሎት አስተባባሪውን ማነጋገር ይችላሉ።

**እንግሊዘኛ መናገር አልችልም፤ እንዴት አድርጌ ለመሥሪያ ቤቱ መደወል እችላለሁ?**

**የትርጉም አገልግሎትን በ13 14 50 ደውለው ቋንቋዎን የሚናገር አስተርጓሚ በመጠየቅ፤ ከኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል ጋር በ (07) 3167 8333 ደውለው እንዲያገናኙዎት መጠየቅ ይችላሉ። የሶስት በኩል የስልክ ግንኙነት ሊካሄድ ይችላል።**


የኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል
519 ኬሰልስ ጎዳና፤(Kessels Road) ማግሬገር
(Macgregor) Q 4109 የፖስታ ሳጥን ቁጥር 6623፤
የላይኛው ማውንት ግራቫት (Mt Gravatt) Q 4122

ስልክ፤ (07) 3167 8333
ፋክስ፤ (07) 3167 8322
በነፃ ጥሪ፤ 1800 188 189 (ከብሪዝበን ከተማ ውጭ)
ኢሜል፤ tccs@health.qld.gov.au


የሥራ ሰአት፡ ከሰኞ-እስከ ዓርብ
8፡30 ጠዋት - 5፡00 ከሰአት በኋላ